የዘካህ ህግጋት

አጭር ማብራርያ

በኪልያስ አህመድ

ዘካህ የስርወ-ቃሉ ቋንቋዊ ትርጉም፦ "መብዛት"፣ "ማደግ"፣ "መጨመር" እንዲሁም "ማመስገን"ና "(ከጉድፈት) ማጥራት"ን የሚያመለክት ነው።

የዘካህ ሸሪዓዊ መልእክት ደግሞ፦ በየተወሰኑ ጊዜያት ከተወሰኑ የንብረት ዓይነቶች ተቆንጥሮ ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች በግዴታነት የሚሰጥ የተገደበ ወጪ ነው።

የዘካህ ድንጋጌ እንደሌሎቹ መሰኮታዊ ህግጋት ሁሉ ከአምልኮ ዘርፍነቱ ባሻገር ድንቅ፣ ብርቅና ፊድቅ ጥበቦችንና ዓላማዎችን ያነገበ ነው። ሰዎች ሊረዷቸው ከሚችሏቸው ግለሰባዊና ማሕበራዊ ጥቅሞቹና የመፍትሄነት ገፅታዎቹ መካከል፦

1. ለችግረኞች መረጃ መሆኑ፣

2. ለድሆች መቋቋሚያ መሆኑ፣

3. በእምነት ላይ የተመሠረተ የጸጸትና የመንፈሳዊነት ትስስርን ማጥበቅ፣

4. ስብዕናን ከስስትና ከንፈግነት ማፅዳት፣

5. ድሆች ለዘብታሞች ያላቸውን ምልከታ ከምቀኝነት ማጥፋት

6. በድህነት ምክንያት የሚፈጸሙ መንጀሎችን መገደብ

7. ከገንዘብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቅል ኢስላማዊ ጉዳዮችን

ለማቀላጠፍ ምክንያት መሆኑና፣

8. የንብረት በረከት ማስከተሉ ጥቂቶቹ ናቸው።

በኢስላም ያለው ደረጃና ብያኔ

ዘካህ ኢስላም ከተገነባባቸው አምስቱ መሠረቶች 3ኛው ሲሆን ለዘካህ በቂ የሆነ ገንዘብ ያለው ማንኛውም ሙስሊም በግዴታነት ዘካህ ማውጣት እንዳለበት በሙስሊሞች መካከል በጥቅሉ ያለምንም ውዝግብ የተፈጋገጠ እውነታ ነው። ይህንን የሚያስገነዝቡት ቁርአናዊና ሀዲሳዊ አስተምህሮቶች በርካታ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ፦

◄ وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ [البقرة: 110]

► «ሰላትንም አቋቁሙ፤ ዘካህንም ስጡ!»

◄ فَإِنْ تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ فَإِخْوَانُكُمْ فِي الدِّينِ [التوبة:11]

►«(ተፀፅትው) ከተመለሱ ሰላትንም ካቋቋሙ ዘካህንም ከሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው።»

◄ عَنْ ابْنِ عُمَرَ – رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا – قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللَّهِ ﷺ: «بُنِيَ الْإِسْلَامُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَالْحَجِّ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ» متفق عليه.

►ዓብዱላህ' ብኑ ዑመር የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል አሉ፦

« ኢስላም በአምስት ነገሮች ላይ ተገነባ፦ ከአላህ በቀር አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን ማቋቋም፣ ዘካን መስጠት፣ ሐጅ ማድረግና ረመዳንን መፆም»[1]

ዘካን ጠቃ የሚያደርግ ባስሀብቶች ሁለት ዓይነት ናቸው:-

1ኛው ዓይነት፦ የዘካህን ግዴታነት ከማስተባበል ጀምሮ ከኩፉትና ከተሰቢት በመነጨ እምቢተኝነት የተነሳ የሚነፍግ ነው፤ ይህ ዓይነቱ ከኢስላም ምንም ድርሻ የሌለው ከዘዲ ስለመሆኑ ጥርጥር የለም።

2ኛው ደግሞ፦ ግዴታነቱን ሳያስተባብል በስስት ጀምሮ በመዘናጋት የተነሳ የሚነፍግ ሲሆን ለእንዲህ ዓይነቱ የሚሰጠውን ብይን አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት ሁለት አመለካከቶች አሏቸው፤

ጥቂቶቹ ይኸኛው እንደመጀመሪያው ከዘዲ መሆኑን ሲናገሩ ብዙሃኑ ግን ወንጅሉ ከባድ ቢሆንም ከኢስላም የሚያስወጣው የክህደት ደረጃ

(1) አል-ቡኻሪ (8)፣ ሙስሊም (16)

አደደርስም ይሳሉ፡፡ መልዕክተኛው ዘካህን የነፈገ በፍርዱ ቀን የሚያጋጥመውን ቅጣት በጠቀሱ ጊዜ፦

◄ «..فيُرى سبيلَه؛ إما إلى الجنة، وإما إلى النار!» رواه مسلم

►«...ከዚያም መንገዱን ይመለከታል (ይጠቆማል)፤ ወይ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት!»[1] ማለታቸው የአብዛኛውን አቋም ይደግፋል፡፡

ዘካህ ግዴታ የሚሆንባቸው መስፈርቶች

የሚከተሉት መሥፈርቶች በሙሉ ካልተሟሉ በስተቀር ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም፤

1. ሙስሊም መሆን ፦ ሙስሊም ያልሆነ ሰው ከዘካህ በፊት ሊያሟላቸው የሚገባ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ስላሉ ዘካህ መስጠት እንደሙስሊም ግዴታ ይሆንበታል አይባልም፡፡ ነገር ግን ሙስሊም ባለመሆኑና ዘካህን ጨምሮ ሌሎች ኢስላማዊ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ፣ እንዲሁም በዝርዝር ጥፋቶቹ መንሰኤነት የወዲያኛው ዓለም ቅጣት እንደሚነባበርበት የሚጠቁሙ ቁርአናዊ መረጃዎች አሉ፡፡

2. ከባርነት ነፃ መሆን ፦ ባሪያም በእጁ ያለው ገንዘብም የኣሳዳሪው ንብረት ናቸውና ዘካህ የማውጣቱ ሃላፊነት ሎሌውን ሳይሆን አለቃውን የተመለከተ ይሆናል፡፡

(1) ሙስሊም (987)

3. **ሙሉ ባለቤትነት** ፦ እንደ «ወቅፁ» ያለ ውስን ባለቤት የሌለው ንብረት ላይ ዘካህ አይደነገግም። በሙሉ ባለተረጋገጠ ባለቤትነት ላይ ያለው ፍርድም ተመሳሳይ ነው።

4. **ንብረቱ «ኒሷብ» (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛው መጠን) መድርሱ**፦ ይህ መጠን እንደንብረቱ አይነት ሊለያይ ይችላል።

5. **ንብረቱ በባለቤቱ ይዞታ ስር ከ«ኒሷብ» ላይንድል በጨረቃ አቆጣጠር አንድ ዓመት መቆየቱ** ፦ ሆኖም ይህ መሥፈርት ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ሦስት ነገሮች አሉ፦

<u>አንደኛው</u>፦ አዝርዕትና ብቅሎች - የዘላ ጊዜያቸው የአዝመሪ መቅት ነውና።

<u>ሁለተኛው</u>፦ ቅድሚያ ከነበረ ግመሎች፣ ከብቶች ወይም በጎችና ፍየሎች የተወለዱ አዳዲስ ግልገሎች፤

<u>ሦስተኛው</u>፦ የንግድ ትርፍ፤

እነዚህ ሦስት የንብረት ዓይነቶች ዓመት ባይሞሳቸውም ሌሎች መስፈርቶች ከተሟሉ የዘካህ ግዴታ ይመለከታቸዋል።

► ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር ለአቅመ አዳም መድረስና የአእምሮ ጤናማነት ያልተጠቀሰበት ምክንያት ፦ ህፃን ልጆች ወይም አእምሮአቸው የታመመ ግለሰቦች ምንም እንኳን ሸፈዓዊ ግዴታዎች በቀጥታ ባይመለከቷቸውም ንብረታቸው ግን «ኒሷብ» እስከደረሰ ድረስ በንብረትነቱ ብቻ ዘካህ ሊጣለት ስለሚገባ ነው፤

የዘካህ ግዴታነት ከንብረቱ እንጂ ከባለንብረቱ ጋር ተያያዥነት የለውምና። ይህ የብዙሀኑ ሲቃውንት አቋም ሲሆን ይህንንም የሚጠቁሙ ንግግሮች ከተለያዩ ሰሃቦች ተዘግበዋል።

የዘካህ ንብረቶች

(ዘካህ ግዴታ የሚሆንባቸው ንብረቶች)

ዘካህ ግዴታ የሚሆነው በጥቅሉ በሰፊት የንብረት አይነቶች ላይ ነው፤ እነሱም ፦

❶- የሚፈሱ ገመሎች፣(የቀንድ) ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች፤

❷- የእርሻ አዝርእትና ሰብሎች፤

❸- የዋጋ ተመን የሆኑ ንብረቶች ማለትም ወርቅና ብር (silver) እንዲሁም የዘመናችን የገንዘብ ኖቶች፤

❹- ለሽያጭ የቀረበ ማንኛውም ሸቀጥና ሰቃ ተመን፤

ዝርዝሩን እነሆ!

1-የሚፈቡ ግመሎች፣ የቀንድ ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች

ከነኚህ እንስሶች ዘካህን መስጠት ግዴታ የሚሆነው በፊት ከተጠቀሱት ጥቅል የዘካህ መስፈርቶች ጋር ሲሎች ቀድመ ሁኔታዎች ሲጨመረ ነው፤ እነሱም፦

1ኛ- አመቱን ሙሉ ወይም የአመቱን አብዛኛውን ክፍል መብላቸው በግጦሽ ስምሪት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። ስለሆነም በአብዛኛው የአመቱ ክፍል በባለንብረቱ ጠጪ የሚዘጋጅ የመኖ ቀለብ የሚመገቡ ከሆነ የዘካህ ግዴታ አይመለከታቸውም ማለት ነው።

2ኛ- እንስሶቹ ለርባታ፣ ለጠተት ወይም ለማደለብ ሰቅድ የተያዙ መሆናቸው ነው። እናም በሞነኛነት ለሥራ የታሰቡ ከሆነ ዘካህ ማውጣት የግድ አይልም ማለት ነው። እንደምሳሌ፦ አንድ ገበሬ ለሸክም ሥራ የሚያከራያቸው ግመሎች ወይም ለእርሻ የሚያጠምዳቸው በሬዎች ቢኖሩት ቁጥራቸው ቢበዛ እንኳ ከነርሱ ዘካህ ማውጣቱ ግዴታ አይሆንም። ለሽያጭ የተዘጋጁ ከሆነ ደግሞ የዘካ አወጣጥ መስፈርቱና ህጉ ወይፈት እንደሚገለፀው ለዮት ይሳል።

3ኛ- እንስሶቹ በሸፈጓ የተገደበላቸውን «ኒሳብ» (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ ቁጥር) የደረሱ ሊሆኑ ይገባል። ይህም እንደ እንስሳው ዓይነት የሚለያይ ሲሆን ዝርዝሩን ቁጥሮ ባሉት ሰንጠረዦች ማስተዋል ይቻላል።

የግመል ዘካህ አወጣጥ

የቤቢ ግመሎቹ ብዛት		ለዘካህ የሚወጣው	
ከ	እስከ	ዓይነት	ብዛት
1	4	-	0
5	9	በግ ወይም ፍየል	1
10	14	በጎች ወይም ፍየሎች	2
15	19	በጎች ወይም ፍየሎች	3
20	24	በጎች ወይም ፍየሎች	4
25	35	አንድ አመት የሞላት ሴት ግመል[1]	1
36	45	ሁለት አመት የሞላት ሴት ግመል	1
46	60	ሦስት አመት የሞላት ሴት ግመል	1

(1) እዚህ ላይ ባለአንድ አመት **ሴት** ግመል ሳይኖረው ባለሁለት አመት **ወንድ** ያለው ያንኑ መስጠት ይችላል።

61	75	ስዒት ስመት የሞሳት ሴት ግመል	1
76	90	ሁስት ስመት የሞሳቸው ሴት ግመሎች	2
91	120	ሦስት ስመት የሞሳቸው ሴት ግመሎች	2

➔ ከ120 በሳይ ያለው ለእያንዳንዱ 40 ግመል ሁስት ስመት የሞሳት ሴት ግመል፤ ለእያንዳንዱ 50 ግመል ደግሞ ሦስት ስመት የሞሳት ሴት ግመል ይከፍሳል።

ለምሳሌ፦

- 130 ግመሎች ያሉት ሰው፦

130 = 40 + 40 + 50

=

አንድ የሁስት ስመት ሴት ግመል	+	አንድ የሁስት ስመት ሴት ግመል	+	አንድ የሦስት ስመት ሴት ግመል

ይህ እስከ 139 ይደቀየርሞ!

- 140 ግመሎች ያለው ሰው፦

140 = 50 + 50 + 40

=	አንድ የሦስት አመት ሴት ግመል	+	አንድ የሦስት አመት ሴት ግመል	+	አንድ የሁስት አመት ሴት ግመል

ይህም እስከ 149 ድረስ አይቀየርም!

- 200 ግመሎች ያሉት፦

200 = 50 x 4 = አራት ባለ ሶስት ዓመት ሴት ግመሎች

= 40 x 5 = አምስት ባለ ሁስት ዓመት ሴት ግመሎች

ስለዚህ ከሁስቱ መንገዶች በመረጠው ዘካህ ያወጣል ማለት ነው።

➔ ከተገዶቱት የሰድሚ ደረጃዎች ያነሰ ጸጸም የበለጠ ብቻ ያለው ባለ ግመል በእያንዳንዱ የአመት ልዩነት ሁለት በጎች ጸጸም ቁየሎችን ለሊያም 20 ዲርሃም ይከፍላል ጸጸም ይቀበላል።[1]

❁❁❁

(1) 20 ዲርሃም ጸደ 59.5 ግራም የሚመዝን ብር (silver) ነው።

የቁንድ ከብት (የላምና የበሬ) ዘካህ አወጣጥ

ለእያንዳንዱ 30 ከብት አንድ አመት የሞላው/ት አንድ ጠንድ ጠይም ሴት ጥጃ ለእያንዳንዱ አርባ ደግሞ ሁለት አመት የሞላት ሴት ከብት ያወጣል።

የርቢ ከብቶቹ ብዛት		ለዘካህ የሚወጣው	
ከ	እስከ	ዓይነት	ብዛት
1	29	-	0
30	39	አመት የሞላው/ት ጥጃ	1
40	59	ሁለት አመት የሞላት ጊደር	1
60	69	አመት የሞላቸው ጥጃች	2
70	79	አንድ ባለ አንድ አመት ጥጃና አንድ ባለ ሁለት አመት ጊደር	2

በዚህ መልኩ ይቀጥላል፤

ለምሳሌ፦

- 80 ከብቶች ያለው ሰው፦

80 = 40 + 40

= ባለ ሁለት አመት ጊደር + አንድ ባለሁለት አመት ጊደር

= 2 ባለ ሁለት አመት

እስከ 89 አይቀየርም!

- 90 ያለው ሰው:-

90 = 3 x 30 = 3 ባለ አንድ አመት ጥጆች

እስከ 99 አይቀየርም!

- ሠላሳ ያለው ሰው:-

100 = 40 + 30 + 30

= አንድ የሁለት አመት ጊደር + ባለአንድ አመት ጥጃ + ባለአንድ አመት ጥጃ

❁❁❁

የከግና የፍየል ዘካህ አመጣጥ

የርኪ በጎች/ፍየሎች ብዛት		ለዘካህ የሚሰጠው	
ከ	እስከ	ዓይነት	ብዛት
1	39	-	0
40	120	በግ ወይም ፍየል	1
121	200	በጎች ወይም ፍየሎች	2
201	399	በጎች ወይም ፍየሎች	3

ከዚህ በኋላ ያለው ቁጥር በ100 በጎች/ፍየሎች ሂሳብ አንድ በግ/ፍየል ይጠላል። ለምሳሌ፦

- 400 በግ ያለው ሰው 4 በግ/ፍየል ያጠላል።

  ይህ እስከ 499 እይቀየርም!

- 500 ያለው አምስት ያጠላል።

➔ ለዘካህ ጠቢ የሚደረጉት በጎች ቢያንስ 6 ወር ፤ ፍየሎቹ ደግሞ አሠት የሞላቸው ሊሆኑ እንድሚገባ በርካታ ዑለማዎች የሚናገረ ሲሆን የተለየ አቋም ያላቸው ሊቃውንትም አሉ።

የእንስሶቹን ዘካህ የተመለከቱ ጥቅል መመፈያዎች

1. ከአንድ በላይ ባለንብረት ያላቸው የዘካህ ከብቶች በአንድ በረት እያደረ በአንድ የጋራ እረኛ የሚሠማረ ከሆነ እንደ አንድ ሰው ንብረት ይታሰባሉ። የዛካህ ህጉም ይህንን የተከተለ ይሆናል።

ለምሣሌ፦ ሁለት ግለሰቦች እያንዳንዳቸው 40 በጎች ቢኖሯቸውና ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ቢደባለቁቸው ዘካህ የሚያወጡት 1 በግ ብቻ ይሆናል። እያንዳንዳቸው 20 ቢኖሯቸውም እንደዚሁ አንድ በግ መስጠት ይኖርባቸዋል። ለዘካህ የሚትሠጠው በግ ከአንደኛው ንብረት ትመሰድና ከሌላኛው የዋጋዉን ግማሽ ይቀበላል።

2. ከሦስት ሁኔታዎች በስተቀር ወንድ ከብቶችን ማውጣት አይቻልም፦
   - ❶ አመት የሞላት ሴት ግመል ያጣ ባለሁለት አመት ወንድ መስጠት ይፈቀድለታል።
   - ❷ በፈና ላም ያለው ባለአንድ አመት ወንድ መስጠት ይፈቀድለታል።
   - ❸ ሴት ከብት ጭራሽ የሌለው ከሆነ ወንድ ማውጣቱ ከችግር አንዳር እንደሚፈቀድለት በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ።
3. ለዘካህ የሚሰጡት ከብቶች በጣም ወድ የሆኑት ወይም በጣም ይተፈለጉት ሳይሆን መለስተኛ የሆኑት ናቸው።
4. የከብቶቹ ቁጥር «ኒሷብ» ከደረሰ በኋላ የሚወለዱ ጥጆችና ግልገሎች ዓመት ባይሞላችውም በዘካህ ሂሳብ ውስጥ ይያመጡሉ። ለምሳሌ፦ 120 በጎች በይዞታው ስር ያሉ ግለሰብ በ11ኛው ወር አንዲት ግልገል ብትወለድለት/ት(!) ከአንድ ወር በኋላ ሁለት በጎችን ለዘካህ ያቀርባል።

2- የእርሻ ሕዝቤቶችና ሰብሎች

የእርሻ ባለቤት የሆነ ግለሰብ ሕዝመፁ በተሰበሰበ ጊዜ ከፌሉን ለዘካህ ጠጪ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ የሚሆነው እንደሌሎች የንብረት ዓይነቶች ዓመት ጠብቆ ሳይሆን በሕዝመፁ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል።

የሕዝርዕትና የጥራጥሬ ዘካህ ግዴታነቱ የሚፀድቀው ከዚህ በፌት ከተጠቀሱት የዘካህ ጥቅል መስፈርቶች ጋር ሌሎች ቅድምና ሁኔታዎች ሲታከሉ ነው።

እነሱም፦

1. ሕዝርዕቱ በመስፈሪያ የሚለካ ወይም መለካት የሚችል መሆኑ፣
2. በመሠረታዊ ምግብነት የሚያገለግሉና ታጉረው ሲቆዩ የሚችሉ መሆናቸው[1]፣

   ➲ በእነዚህ ሁለት መሥፈርቶች መሠረት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ምስር፣ ተምር፣ ዘቢብ ካሉ እህሎች፣ ጥራጥሬዎችና ፍሬዎች ዘካህ ሊጠጣ እንደሚገባ እንረዳለን፤ በአንፃሩ ደግሞ እንደ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ካሮት፣ ጎመንና ሽንኩሩ ባሉት ቅጠላ ቅጠሎችና ፍራፍሬዎች ላይ ዘካ ግዴታ እንደማይሆን እንገነዘባለን።
3. ሕዝርዕቶቹና ሰብሎቹ በግለሰቡ ይዞታ ስር ሆነው ለሕዝመፁ መድረሳቸው፣

(1) ይህንን መስፈርት የማይቀበሉ በርካታ ሊቃውንት አሉ!

ለምሳሌ፦ አዝመሬው ከደረሰ በኋላ (ባደለበሰብ እንኳ) አዝርዕቱን በስጦታ ወደም በግዢ፣ አሊያም በውርስ ያገኘ ሰው ዘካውን የማውጣት ግዴታ የለበትም፤ ግዴታው በቀድሞው ባለቤት ላይ ይሆናልና! ለአዝመሬ ከመድረሱ በፊት የተረከበ እንደሆነ ግን አዝመሬው ሲደርስ ግዴታው ይመለከተዋል።

4. አዝርዕቱ ከተጣቃ በኋላ መጠኑ ቢያንስ 1200 የሁለት ሰጅ ስፍር መሙላቱ፣ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሸሪዓዊ ገደብ ስፍርን የተመረኮዘ እንጂ ክብደቱን የተመለከተ እንዳልሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። የተከበረት መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፦

◄ «ليس فيما دون خمسة أوسق صدقة»

► «ከአምስት "አውሱቅ" በታች ሰደቃ የለም»[1]

- 1 ወሰቅ = 60 ሳዕ[2]፤ 1 ሳዕ = 4 የሁለት ሰጅ እፍኞች
- 5 አውሱቅ = 5x60ሳዕ = 300ሳዕ = 300x4 እፍኞች = 1200 እፍኞች

ይህም ከሞላ ጎደል በደህና የስንዴ ስፍር ሲሰላ በትንሹ 612 ኪ.ግ አካባቢ ይመዝናል። ሆኖም የስፍሩ ክብደት እንደየአከሱ አይነት የሚለያይ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

(1) አል-ቡኻሪ(1447)፣ ሙስሊም(979)(980)
(2) በድሮ ጊዜ የነበረ የእህል መስፈሪያ ነው።

➔ እህሉ እጅ በእጅ ባደሰፈር እንኳ ከአዝመሪው በፌት ልምድ ባላቸው ታማኝ ሰዎች መጠኑ ሲገመት እንደሚችል ብዙሀኑ ሲቃውንት ይስማማሉ። ታዲያ በዚህ መልኩ ሲለካ 1/3ኛውን ወይም 1/4ኛውን ከሂሳቡ ማቃለል እንደሚገባ የሚጠቁም ሐዲሥ ቢኖርም በርካታ ሲቃውንት ዘገባው ጠንካራ እንዳልሆነ ያጠሳሉ።

❁❁❁

ለዘካህ ጠቢ የሚሆነው መጠን

አዝርዕቱ ከላይ የተጠቀሰው የስፍር መጠን ያህል ከደረሰ ተሰፍሮ ጠቢ የሚሆነው የዘካህ መጠን እንደሚከተለው ይገለፃል፦

➢ እርሻው በዝናብ፣ በወንዝ ወይም በመስኖና በመሳሰሉት ዘዴዎች ውሃ የሚያገኝ ከሆነ ከተሰበሰበው አንድ አስረኛው (10%) ለዘካህ ይሰጣል፤ እነዚህ ላይ የሚታየው ውሃ ለማጠጣት ተያጋጊ ልፋት አለመኖሩ ነውና!

➢ ማሳው የገበፌውን ተያጋጊ ልፋት በሚጠይቁ የውሃ ማጠጫ ዘዴዎች ውሃ የሚያገኝ እንደሆነ ግን አንድ ሃያኛውን (5%) ብቻ ጠቢ ያደርጋል። ይህ ውሃን በተለያዩ ዘዴዎች በመቅዳት፣ ወይም በዘመናዊ መሣሪያዎች ወደ እርሻው በማስተላለፍ የሚካሄደውን የማጠጣት ስልት ያካትታል።

የአዝርዕቱን ዘካህ የተመለከቱ ጥቅል መመሪያዎች

➔ የተለያዩ የእህልና የአዝርዕት ዓይነቶች ለየብቻ ሲሰፈሩ በተናጠል «ኒሷብ» ካልደርሱ ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም፡፡

➔ በኪሩይ ወይም በተለየ ውል በሌላ ሰው መሬት ላይ እህል የዘሩ ግለሰብ የዘካህ ግዴታ ይመለከተዋል፤ የእህሉ ባለቤት እርሱ ነውና፡፡ የመሬቱን ባለቤት የአዝርዕቱ ዘካህ አይመለከተውም፡፡

❁❁❁

3-እንዴ ወርቅና ብር ያሉ የዋጋ ተመኖች ዘካህ

የወርቅና የብር ማዕድናች በቀድሞው ዘመን ዋነኛ መገበያያና የተመን መለኪያ ሆነው ቆይተዋል። ስለሆነም ለዘካህ የደረሰ የወርቅ ወይም የብር (ሲልቨር) መጠን ናሮት በጨረቃ አቆጣጠር አመት ያሳለፈ ሙስሊም የተወሰነውን ያህል ወጪ ማድረግ እንደሚገባው በሸሪዓችን ፀድቋል።

- ወርቅን አስመልክቶ ፦ ቢያንስ 20 ዲናር (ሚሥቃል) ያለው ሰው ከአመት በኋላ 1/40ኛውን (ወይም 2.5%)ለዘካህ ወጪ ማድረግ አለበት።

20 ዲናር (ሚሥቃል) በዘመናችን መለኪያዎች ሲገለፅ እንደሚከተለው ይሆናል፦

1 ዲናር ወርቅ = 4.25 ግራም (በብዙሀኑ አቋም)

20 ዲናር = 85 ግራም

✸ እናም የወርቅ «ኒሷብ» (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ መጠን) = 85 ግራም ነው ማለት ነው።

- የብር ማዕድንን አስመልክቶ ፦ ቢያንስ 200 ዲርሀም ያለው ሰው በአመቱ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካ ወጪ ማድረግ ይኖርበታል።

200 ዲርሃም በዘመናችን መለኪያዎች ሲገለፅ እንዲሚከተለው ይሆናል፦

1 ዲርሃም = 2.975 ግራም (በብዙሀኑ አቋም)

200 ዲርሀም = 595 ግራም

✸ እናም የብር (ሲልቨር) «ኒሳብ» 595 ግራም ይሆናል ማለት ነው።

➔ከሴላ ማዕድን ጋር የተቀየጠ ወርቅ ወደሃ ብር ቅደሙ ስመዛኙን መጠን የያዘ እንደሆነ ወርቁ ወደሃ ብረ ስብቻው የሚኖረው የተጣራ ክብደት «ኒሷብ» ካለደረሰ ዘካህ ማውጣት ግዴታ አደለውንም። የቅደሙ መጠን በጣም አነስተኛ ከሆነ ግን የወርቁ/የብረ የተጣራ ክብደት ስብቻው የኒሷብ መጠን ባደኖረው እንኳ በድምረ የኒሷብ መጠን ከደረሰ አስጠቃላዩ ዘካህ ማውጣት የግድ እንደሆነ የሚናገረ ሊቃውንት ስት። ሌሎች ደግሞ እንደመጀመሪያው የተጣራው ንጹህ ወርቅ/ብር ስብቻው እንደሚሰላ ደናገሩት፤ በዚሁ መሠረት፦

ባስ 24 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 85 ግራም

ባስ 21 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 97.14 ግራም

ባስ 18 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 113.3 ግራም

➔ ወርቅ እና ብር የተስያዩ ሸቀጣዊ ብደኖች ያሏቸው በመሆኑ በዘካህ ላደ የተስያየ ሂሣብ ደሰላላቸዋል እንጂ አንድ ላደ አደደለውም ::

➔ በሸቀጣ በተፈቀደ መልኩ እንደ ገጥ የሚያገለግል የሴቶች ወርቅንና ብርን አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት የተስያዩ አመለካከቶች አሏቸው። ጥቅል ቁርአናዊና ሀዲሣዊ አስረጃች የሚደግፉት አቋም መጠኑ "ኒሷብ" እስከደረሰ ድረስ ዘካህ በየዓመቱ ማውጣቱ የግድ መሆኑን ነው።

❁❁❁

የገንዘብ ዘካህ

በዘመናችን የዋጋ ተመንነትን ተክቶ የሚገኘው የገንዘብ ኖትን አነሳስና ታሪካዊ ሂደት የተመለከቱ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል። በሉኑ ወቅት ሊሠጠው የሚችለውን ሸሪዓዊ ብይን አስመልክቶም የተለያዩ አስተያየቶች ተሠንዝረዋል። ዳሂ ግን የኢኮኖሚው ዓለም ተጨባጭ ሂደት የሚያስረዳው የገንዘብ ኖት የግብይት ዋነኛ መሣሪያ መሆኑ በተዘዋዋሪ ከወርቅና ከብር ጋር ቢያመሳስለውም ራሱን የቻለ የዋጋ ተመን መሆኑን ነው።

ስለሆነም «ኒሷብ» የደረሰ የገንዘብ መጠን ኖሮት አመት ያሳለፈ ሙስሊም ከገንዘቡ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካህ መክፈሉ የግድ ይሆናል።

ታዲያ ዘካ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ የገንዘብ መጠን (ኒሷብ) የሚገደብበት መሠረት የወርቅ ዋጋ ወይስ የብር? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ብዙሀኑ የዘመናችን ሊቃውንት የመረጡት ሚዛን ደፊ ቅሄም በመቅቱ ከሁለቱ የኒሷብ ዋጋዎች አነስተኛ በሆነው ላይ እንደሚሆን ነው።

ለምሳሌ፦➢ ዘካህ በሚጣልበት ወቅት የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 500 ብር ቢሆን ይህንን በ85 ስናበዛው የወርቅ ኒሷብ ዋጋ ይሰጠናል፦

➲ 500 x 85 = 42,500 ብር ይሆናል፤

➢ የብር (ሲልቨር) ዋጋ ደግሞ በግሬም 25 ብር ቢሆን ይህንን በ595 ስናበዛው የኒሷቡን ዋጋ ይሠጠናል፦

➲ 25 x 595 = 14,875 ይሆናል፤

ይህ ውጤት ከወርቁ የኒሷብ ዋጋ ያንሳል። በመሆኑም የገንዘብ ኖት ዘካህ በብር ዋጋ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ ያለው ተመን የሚያሳየንም የብር ኒሷብ ዋጋ ከወርቅ ኒሷብ ዋጋ እጅግ እንደሚያንስ ስለሆነ ቢያንስ 595 ግሬም ብር የሚገዛ የገንዘብ መጠን ያለው ባለሀብት 1/40ኛውን (2.5%) ዘኪ ማድረግ ይጠበቅበታል።

❁❁❁

4-የንግድ ዘካህ

ለሽያጭ የቀረበ ማንኛውም ሸቀጥና ሰቃ ድምር ተመኑ ከላይ የተጠቀሰውን የጥፌ ገንዘብ «ኒሷብ» የሚያክል ከሆነ ዓመት በሞላው ጊዜ ከዋጋው 1/40ኛውን ለዘካህ መውጣት ይኖርበታል።

የንግድ ዘካህን አስመልክቶ ማስተዋል የሚሹ በርካታ ነጥቦች አሉ፦

1. የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚሆነው <u>ለሽያጭ በተዘጋጁ</u> ንብረቶች ዋጋ ላይ ብቻ ነው። በዚህም መሠረት ለንግዱ ተግባር አጋዥ የሆኑ ማሽኖች፣ ማመላለሻ መኪናዎች፣ ታክሲዎች፣ ለኪራይ የተዘጋጁ ንብረቶችና የመሳሰሉት የዘካ ግዴታ አይመለከታቸውም። ሆኖም ከነዚህ የሚገኘው የገንዘብ ገቢ ለዘካህ ብቁ ሆኖ ዓመት ከሞላው እንደማንኛውም የዘካህ ንብረት ይታያል።

   ➔ ወደ ሸቀጥነት ተቀይረው ለሽያጭ የሚቀርቡ ጥፌ ሰቃዎች በጥፌ ሰቃነታቸው ዋጋቸው ተተምኖ ዘካህ ሊወጣላቸው ይገባል።

2. የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በቀረቡት ንብረቶች <u>ድምር ተመን/ዋጋ</u> ላይ እንጂ በንብረቶቹ ፈላቸው ላይ አይደለም። በዚህም መሠረት፦

   2.1 እንደ ከብቶችና ወርቅ ያሉ ሌሎች የዘካህ ንብረቶች ለሽያጭ ከቀረቡ የሚመለከታቸው <u>የንግድ ዘካህ ብቻ መሆኑን ብዙ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ</u>፤ ስለሆነም ዋጋቸው ተተምኖ የንግድ

«ኒሷብ» ከደረሰ 1/40ኛው ወጪ ደሆናል እንጂ ሌላ ግዴታ አይመለከታችውም።

2.2 በንግዱ ዓለም ለሽያጭ የቀረቡ ንብረቶች እየተሸጡ በሌላ መተካታቸው የተለመደ ነውና <u>ሸቀጦቹ ፈሳቸው አመት ሲሞላቸው የግድ አይልም</u>፤ ዘካው የተያያዘው ከሸቀጦቹ ካፒታል/ዋጋ ጋር ነውና።

2.3 የንግድ ዘካህ ሲሰላ <u>ከሌላ ጥፌ ገንዘብ ጋር ተደምሮ መሆን ይገባዋል</u>። ይህ ገዜውንም (የዘካህ ዓመቱን)፣ መጠኑንም (ኒሷቡንም) የሚመለከት ነው። ለምሣሌ፦ አንድ ሰው ለዘካህ የደረሰ ጥፌ ገንዘብ በረመዳን ወር ቢያገኝና አመት ሳይሞላው በተመሰነው ገንዘቡ ለንግድ የሚሆኑ ሸቀጦችን ቢገዛ በዘካው ሳይ የሚያስከትለው ለውጥ የለም፤ በሚቀጥለው ረመዳን ወር የሸቀጦቹን ድምር ተመን አውጥቶ ከተረፈው ጥፌ ገንዘብ ጋር በማደበል ዘካህ ያወጣል። እንደዚሁም፦ አንድ ሙስሊም ጥፌ ገንዘብና ሌላ የንግድ ሸቀጥ ፍርት ሁለቱም እያንዳንዳቸው ኒሷብ ያልደረሱ ሆነው የሁለቱ ድምር ኒሷብ ቢሞላ ከድምሩ ዘካህ ማውጣት ይጠበቅበታል።

3. የንግድ ሸያጭ <u>ትርፍ</u> ዘካህ መታሰብ የሚጀምረው ለሸያጭ ከሚቀርበው ሸቀጥ ካፒታል መነሻ ስለሆነ <u>አዲስ የዘካህ አመት አይጀመርለትም</u>።

ለምሣሌ፦ አንድ ባለሀብት በአመቱ መጀመሪያ በ100 ሺህ ብር ሸቀጦችን ሸምቶ ንግድ ቢጀምርና በአመቱ መጨረሻ የ30ሺህ ብር ትርፍ ቢያገኝ ዘካህ የሚያወጣው ከ130 ሺህ ብር ይሆናል። ኪሳራም ቢያጋጥመው

እንዲሁ በአመቱ መጨረሻ ያለውን ንብረት መጠን ተምኖ 1/40ውን ማውጣት ብቻ ነው የሚኖርበት፤ የ100 ሺህ ብር የንግድ ሸቀጥ ገዝቶ በአመቱ ማብቂያ የ20 ሺህ ብር ኪሳራ ቢደርስብት ዘካ የሚያወጣው ከ80 ሺህ ብር ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

► በመሆኑም ለሽያጭ የቀረበው ንብረት ዘካህ ሲሰላ የሚታሰበው ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ ሳይሆን በዘካው ወቅት የሚሸጥበት ዋጋ መሆኑን ማስተዋል ያሻል፡፡

➔ የንግድ አክሲዮን ባለቤት የሆነ ግለሰብ የአክሲዮኑ ድርሻ የሚወክለውን የሽያጭ ዕቃ ተመንና ትርፍ ከሌላ ጥሬ ገንዘብ ጋር ደምሮ በማስላት ዘካህ ያወጣለታል፤ ድርጅቱ የአክሲዮኖቹን ዘካህ የሚያወጣ እንደሆነ ግን ግለሰቡ ዳግም ወጪ አይጠበቅበትም፡፡

❁ በመሬት ውስጥ ተቀብሮ የተገኘ የድሮ ቅርስ (ሬካዝ) ቀድሞ የሙስሊም ንብረት እንደነበር የሚጠቁም ምልክት ካለው ለጠፋ ንብረት የሚሰጠው ኢስላማዊ ብይን ይኖረዋል፤ ካልሆነ ግን ጥቅል መጠኑ ይነስም ይብዛም 1/5ኛው (20%) ወጪ ይሆናል፡፡ ሆኖም የተገደበ የኒሷብ መጠን የሌለው ከመሆኑ፣ ከወጪ አደራራጉና ከሌሎች ሁኔታዎች አንፃር በዘካህ ህግ ስር የማይካተት መሆኑ የብዙሀኑ ሊቃውንት አቋም ነው፡፡

❁❁❁

የዘካ አጠጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

1. ዘካን በየአመቱ ማውጣት

ከአዝርዕት በስተቀር ያሉ የዘካ ንብረቶች ከ«ኒሷብ» እስካልጎደሉ ድርስ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየአመቱ የዘካህ ጠጪ ይመለከታቸዋል።

2. ዘካህና ዕዳ

ዕዳ በዘካህ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት የተለያየ አቋም ይዘዋል። ሆኖም ሚዛን የሚደፋውን አመለካከት መጥቀሱ በቂ ይሆናል፤

2.1 ዕዳ ያለበት ሰው ዕዳውን የሚከፍልበት ጊዜ ካልደረሰ በስተቀር ከዘካህ ሒሳቡ ላይ ዕዳውን አይቀንስም። ምክንያቱም በእጁ ባለው ገንዘብ መጠቀም እስከቻለ ድረስ ዘካውን የማውጣት ሐላፊነት ስለሚኖርበት ነው። ዕዳውን የሚመልስበት ወቅት ከደረሰ ወይም ከቀረበ ግን መጠኑን ቀንሶ ሒሳቡን ያሰላል።

2.2 ሌላ ሰው ዘንድ የዕዳ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ደግሞ በፈለገው ጊዜ በእጁ የሚያገኘውና የሚጠቀምበት ባለመሆኑ ገንዘቡ እስኪመለስለት ድረስ ዘካህ የማውጣት ግዴታ አይኖርበትም፤ በአንድ ንብረት ላይ ሁለት ዘካህ አይጠየቅም! ሆኖም ገንዘቡ የሚመለስበት ጊዜ ደርሶ ባለዕዳው ዕዳውን ለማስረከብ ዝግጁ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ የዘካህ ሒሳቡ በባለንብረቱ ላይ የሚታሰብ ይሆናል።

3. ዘካህና ወርሀዊ ገቢ

ለዘካህ የደረሰ የንብረት መጠን ኖሮት ዓመት ሳይሞላው ሌላ ጭማሬ ያገኘ ግለሰብ ያገኘው የንግድ ትርፍ መያዙ ከቀድሞ ከብቶች የተወለደ ግልገል እስካልሆነ ድረስ አዲስ የዘካህ ዓመት ይጀምርለታል።

➔ በዚህም መሠረት ገቢውን የሚያጠራቅም ደሞዝተኛ ጥርቅሙ የዘካህ ኒሳብ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ አመት መቁጠር ይጀምራል። ከዚያ በኋላ በየወሩ የሚያገኘው ደሞዝ ለየብቻው ኒሳብ ባይሞላ እንኳ አመት ሲሞላው 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካህ ወጪ ያደርጋል።

ይህ መንገድ ለእያንዳንዱ ወር አዲስ ሒሳብ በማስላት ከአመት በኋላ በየወሩ ዘካህ ማውጣት ስለሚያስፈልገው አፈፃፀሙ ለብዙዎች አስቸጋሪ ይሆናል።

➔ ስለሆነም ቀላልና ገር የሆነው መንገድ በአመቱ መጨረሻ ላይ በእጅ ያለውን ገንዘብ ባጠቃላይ በማስላት 1/40ኛውን ማውጣት ነው። በዚህ ጊዜ የተወሰነው የገንዘብ መጠን አመት ሳይሞላው በቅድሚያ ዘካህ ይጠላለታል ማለት ነው።

ዘካህ የሚሠጣቸው ወገኖች

የዘካህ ድንጣ የሚገባቸው ወገኖች ስምንት ዓይነት ናቸው። እነርሱም በሚከተለው የአላህ ቃል ተዘርዝረዋል፦

◄ إِنَّمَا الصَّدَقَاتُ لِلْفُقَرَاءِ وَالْمَسَاكِينِ وَالْعَامِلِينَ عَلَيْهَا وَالْمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمْ وَفِي الرِّقَابِ وَالْغَارِمِينَ وَفِي سَبِيلِ اللَّهِ وَابْنِ السَّبِيلِ فَرِيضَةً مِنَ اللَّهِ وَاللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ

[التوبة: ٦٠]

►« (ግዴታ) ምፅዋትም ለድሆች፣ ለምስኪኖች፣ በሷም ላይ ሠሪዎች ለሆኑ፣ ልቦናቸው (ኢስላምን)የሚላመድ፣ በባሮችም፣ በባለዕዳዎች፣ በአላህም መንገድና፣ (ካገሩ ለወጣ) መንገደኛ ነች፤ ከአላህ ዘንድ (የተገደበች) ግዴታ፤ አላህም እጅግ አዋቂ፣ ጥበበኛ ነው።»

ሣብሬፈያው እንዲሚከተለው ደጠቀሳል፦

1. ድሆች፦ ድሆች የሚባሉት የእለት ጉርሳቸውን በበቂ መልኩ የማያገኙ ናቸው። ዘካህ ሲከፋፈል ቢቻል የመሥሬት ስቅም ሳሳቸው ከድህነት ወጥተው የሚቋቋሙበት፣ ስቅሙ ለሌሳቸው ደግሞ ለስመት የሚበቃቸውን ያህል ቢሰገሱ ደመረጣል።
2. ምስኪኖች ፦ ምስኪኖች የሚባሉት ስስፈሳጊ የኑሮ ሣሚያዎችን የማያገኙ ናቸው።[1]

(1) በድሃ(الفقير)ና በምስኪን(المسكين) መካከል ያለውን የትርጉም ልዩነት አስመልክቶ በርካታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል።

3. **የዘካህ ሰብሳቢዎችና አከፋፋዮች፦** እነርሱም የሙስሊሞች የበላይ መሪ ዘካህን እንዲሰበስቡና እንዲያከፋፍሉ የመደባቸው ሲሆኑ ለዚህ ስራቸው ከዘካህ ገንዘብ አበል ይቆረጥላቸዋል።

4. **ልቦናቸው (ኢስላምን) የሚላመድ፦** እነኚህም ኢስላምን ለመቀበል ዝንባሌ ያላቸው፣ ጀምሮ አዲስ ሰለምቴዎች ሆነው እምነታቸው ያልጠነከረ ግለሰቦች ሲሆኑ የዘካህ መልካም አድራጎት ለእምነታቸው መስተካከልና መሻሻል አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ከተገመተ ከዘካህ ጠጪ ውስን ድርሻ ይኖራቸዋል።

5. **በባርነት ሥር ያሉ ሙስሊም ጠገኖች፦** በባርነት የሚገዙ ሙስሊሞችን ገዝቶ ነፃ ለማውጣት ጀምሮ በተወሰነ ክፍያ ነፃነታቸውን ለማግኘት ከአሳዳሪዎቻቸው ጋር ውል የፈፀሙትን በክፍያ ለማገዝ ከዘካህ ገንዘብ ጠጪ ይደረጋል።

➔አንዳንድ ሊቃውንት ምርኮኛን ለማስለቀቅ የሚከፈል ቤዛ በዚሁ ፍርድ ውስጥ እንደሚካተት ይናገራሉ።

6. **ባለዕዳዎች፦** ዕዳ ተሸክመው መክፈል የተሳናቸው ጠገኖች ዕዳቸውን መክፈል የሚችሉበት የገንዘብ መጠን ከዘካህ ይሰጣቸዋል።

ባለዕዳዎች ሁለት ዓይነት ናቸው፤

❶ ለግል ጥቅማቸው ጀምሮ በግል ጥፋታቸው ምክንያት ዕዳ የተጫነባቸው፣

❷ በሰዎች መሀል የሚከሰት ጠብን ለማብረድ የንብረት ዋስትና የተሸከሙ፤ እንደነዚህ ዓይነቶቹ የግል ሀብት ቢኖራቸውም ለዘካህ ድጋፍ ተገቢ ናቸው።

➔ ሌላ ሰው ዘንድ በሷጻ መልክ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ዘካህን በመስጠት ሷላቤ ገንዘብ ሳያጠጣ ከባለሷጻው ሷጳን ማቃለል ጀምሮ መሰረዝ የፌስን ጥቅም መጠበቅ ነውና እንደዘካህ አይፈይድም።

7. **በአላህ መንገድ ላይ ታጋይ የሆኑ፦** ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ተቸሯቸው የሌላቸው ታጋዮች ለ«ጂሃድ» የሚያስፈልጋቸው ጠቃ ከዘካህ ይሰጣቸዋል። ብዙሀኑ ሊቃውንት ይህ መልዕክት የተጠቀመበት ቁርዓናዊ ቃል (وَفِي سَبِيلِ اللَّه) ሌሎች ሰናይ አድራጎቶችን እንደማያካትት አስረግጠው ይናገራሉ። በዚህም መሠረት መስጂድ ለመገንባት፣ ት/ቤቶችን ለማቋቋም፣ ጠቃሚ መፅሐፍትን አትሞ ለማሰራጨት፣ የሕክምና ማዕከላትን ለመመሥረትና ለመሳሰሉት የበጎ ተግባር መስኮች የዘካህ ገንዘብን ማዋል የማይፈቀድ ይሆናል ማለት ነው። ሆኖም ብዙ ሊቃውንት ለኢስላማዊ እውቀት ፍለጋ ጊዜያቸውን የሰጡ ተማሪዎች እንደ ታጋዮች የዘካህ ድርሻ እንደሚገባቸው ያሰፍራሉ።

8. **ጠያ አገረ የሚመለስበት ጠቃ ያጣ መንገደኛ፦** እንዲህ ዓይነቱ በመኖሪያ አገረ በቂ ሀብት ቢኖረው እንኳ ጠያ አገረ መመለሻ የጉዞ ጠቃ ከዘካህ ገንዘብ ይሰጠዋል።

❁❁❁

የዘካህ አሰጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

1. ዘካህን ለዘመድ መስጠት፦ ማስተዳደሪ ግዴታ ላልሆነ ዘመድ ዘካህን መስጠት ይፈቀዳል። ወጪያቸውን መሸፈን ግድ ለሚል የቅርብ ዘመዶች መስጠቱ ግን ወጪን በማስቀረት እፈስን መጥቀም በመሆኑ የተከለከለ ይሆናል። በዚህም መሠረት ለወላጆች፣ ለልጆችና ለሚስቶች ዘካህ መስጠት ይከለከላል።
2. የአላህ መልዕክተኛ ቤተሰቦችና ዝርያዎች፦ የዘካ ገንዘብን መቀበል አይችሉም።
3. ሙስሊም ላልሆነ ሰው ዘካህ መስጠት አይቻልም። ከዘካ ውጪ ያለ ተፈ ምፅዋት መሰጠት ግን አይከለከልም ።
4. ዘካህ ግዴታ የሆነበት ሰው ወቅቱ ከደረሰ በኋላ በቂ ምክንያት ሳይኖር ማዘግየት የለበትም።
5. የሁለት ዓመት ዘካህ አስቀድሞ ማውጣት እንደሚፈቀድ የሚያሳይ ሀዲሣዊ መረጃ አለ።
6. ዘካህን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ማሻገር፦ ይበልጥ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ እንዲሚፈቀድ በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ።

ተፈጸመ!!

ዘካተል ፈጥር እና አፈጻጸሙ

በጣሀ አህመድ

ዘካተል ፈጥር ከረመዳን ወር ፃም መጠናቀቅ ጋር በተያያዘ ግዴታ የሚሆን የዘካ አይነት ነው።ዘካተል ፈጥርን መስጠት እያንዳንዱ ሙስሊም ሳይ በነፍስ ወከፍ ግዴታ ሲሆን፤ እያንዳንዱም አባወራ የራሱን ጨምሮ በእርሱ ስር ስላሉ ቤተሰቦቹ ሁሉ መስጠት ይጠበቅበታል። ኢብኑል ሙንዚር 'አል-ኢጅማዕ' በተሰኘው ኪታባቸው **‹‹ዒልምን የተማርንባቸው ዑለማዎች ሁሉ ዘካተል ፈጥር ግዴታ መሆኑን ተስማምተውበታል››** በማለት የጉዳዩን ግዴታነት ከሚያመለክቱት ነብያዊ ሀዲሶች በተጨማሪም የኡለማዎችን አጠቃላይ ስምምነት (ኢጅማዕ) የተገኘበት መሆኑን ጠቁመዋል።

የተደነገገበት ጥበብ

ድሆች በባዕሉ (ዒድ) እለት ሰዎችን ከመለመን እንዲድኑና የእለቱ ደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በፃም ወቅት ተከስተው ሳለፉ አንዳንድ ጉድለቶች (ግድፈቶች) ማሟያ እንዲሆን ነው። ይህን አስመልክቶ ዐብደላህ ኢብን አባስ እንዲህ ይላሉ።

عن ابن عباس ـ رضي الله عنهما ـ قال: "فرض رسول الله صلى الله عليه وسلم زكاة الفطر طهرة للصائم من اللغو والرفث وطعمة للمساكين، فمن أداها قبل الصلاة فهي زكاة مقبولة، ومن أداها بعد الصلاة فهي صدقة من الصدقات" رواه أبو داود وابن ماجه

‹‹የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዘካተል ፈጥርን ለፃመኛ ለ 'ለግዉ' (ጥቅም ለሌላቸው ውድቅ የቀልድ ንግግሮችና ተግባሮች) እና ለ 'ረፈስ' (ፃታዊ ለሚትን ቀስቃሽ ለሆኑ ንግግሮች) ማፅጃ፤ ለምስኪኖች (ድሆች) መብል ሲሆን በግዴታ መልኩ ደንግገውታል። ስለዚህም ከዒድ ሰላት በፊት (ዘካውን በመስጠት ግዴታውን የተወጣ) ተቀባይነት ያለው ዘካን ሰጥቷል፤ ከዒድ ሰላት በኋላ ዘካውን የሰጠ ከሌላ ግዴታ ያልሆነ ሰደቃ ሰንዱ እንደሆነ ይታሰብለታል።›› (አቡዳውድ እና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)

የዘካተል ፊጥር መጠን

ኢብኑ ኡመር ሀዲስ ላይ እንዲህ የሚል መልዕክት ስለተላለፈ ነው **‹‹የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) ከተምር ወይም ከገብስ አንድ ‹‹ሳዕ›› በእያንዳንዱ ሙስሊም፤ ባሪያ፣ ጨዋ (ባሪያ ያልሆነ)፣ሴት፣ ህፃን፣ አዋቂ ላይ ግዴታ አድርገዋል። እንዲሁም ሰዎች ወደ (ዒድ) ሰላት ከመውጣታቸው በፊት ለሚገባቸው ሰዎች እንዲደርስ አዘዋል።››**

(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ሳዕ የመስፈሪያ አይነት ሲሆን በድሮ ጊዜ የነበረ የእህል መስፈሪያ ነው። በዘመናዊ መስኪያ አንድ ‹‹ሳዕ›› 2.04-2.5 ኪ.ግ ይመዝናል።

1 ሳዕ = 4 የሁለት እጅ እፍኞች ነው።

ዘካተል ፊጥር በማን ላይ ግዴታ ይሆናል?

ዘካተል ፊጥር ግዴታ የሚሆነው ሁለት መስፈርቶችን ባሟላ ሰው ላይ ብቻ ነው፤ እነርሱም

1. ሙስሊም በሆነ
2. ዘካተል ፊጥር ማውጣት ግዴታ በሚሆንበት ቀን እና ሌሊት፤ ለራሱ እና ለቤተሰቦቹ የሚበቃ መብል ኖሮት የተረፈው እና ተጨማሪ ነገር ያለው።

ዘካተል ፊጥር የሚሰጠው መቼ ነው?

ዘካተል ፊጥርን ከ(ዒድ) ሰላት በፊላ ማዘግየት የተከለከለ ሲሆን፤ ማውጣቱ ግዴታ የሚሆንበት ወቅት የሚጀምረው ከረመዳን የመጨረሻው እለት ፀሀይ ከጠለቀችበት ወይም ዒድ መሆኑ ከተረጋገጠበት ሰዓት አንስቶ ነው። ነገር ግን ኢብኑ ዑመርን ጨምሮ ሌሎችም ሰሀቦች ያደርጉት እንነበረው ከዒድ አንድ ወይም ሁለት ቀን ቀድሞ ዘካተል ፊጥርን ማውጣት ይፈቅዳል።

ሰዎች ለዘካተል ፊጥር የሚሰጡ የእህል አይነቶች

ዘካተል ፊጥር ሙስሊሞች ከሚመገቡዋቸው እንደ አሩዝ፤ በቆሎ፤ ጤፍ.... ባሉ የምግብ እህል አይነቶች ነው። መልእተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) በሀዲስ የጠቀሷቸው የምግብ እህሎች (እንደ ገብስ፤ ተምር፤ ዘቢብ) የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ ነገር ግን የምግብ አይነቶቹ በነዚህ ላይ ብቻ እንደማይገደቡ የሻፊዒያ እና የማሊኪያ መዝሀብ ዑለማዎች ሲስማሙበት ሸይኹል ኢስላምም የመረጡት አቂም ነው።

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) ከተምር ወይም ከገብስ አንድ ‹‹ሷዕ›› እንዲወጣ ማዘዛቸውን በተመለከተም እነዚህ ዑለማዎች የሚሰጡት ምላሽ ‹‹**መልእክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) እነዚህን የምግብ አይነቶች የጠቀሱት የመዲና ሰዎች በምግብነት ይጠቀሟቸው የነበሩ ከመሆናቸው አንፃር ነው። ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) እነሱ የሚያገኙትንና የሚመገቡትን የምግብ አይነት ነው እንዲያወጡ ያዘዟቸው**›› የሚል ነው። በዚህም መሰረት በማንኛውም አካባቢ የሚኖር ሙስሊም ማህበረሰቡ አዘውትሮ ከሚመገባቸው የምግብ እህሎች ዘካተል ፊጥሩን መልዕክተኛው ሲጠቀሙበት በነበረው መስፈርያ መጠን ማውጣት ይችላል።

ዘካተል ፊጥር መሰጠት የሚገባው ለማን ነው?

በዚህ ጉዳይ ላይ ዑለማዎች ሁለት አይነት አመለካከት ያለቸው ሲሆን ሚዛን የሚደፋው ሀሳብ ለምስኪኖች እና ለድሆች ብቻ ይሰጣል የሚለው ነው። ምክንያቱም በኢብኑ አባስ ሀዲስ ላይ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) ‹‹**ለምስኪኖች መብል** ...›› በማለት ዘካተል ፊጥር የተደነገገበትን አላማ ከመግለፃቸው ጋር የተያያዘ ነው።

ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ ተምኖ መክፈል

ዘካተል ፊጥርን በዋጋ ተምኖ መክፈል አይፈቀድም። ምክንያቱም በሲብኑ አባስ ሀዲስ ላይ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) ዘካተል ፊጥር የተደነገገበትን አላማ ሲገልፁ ‹‹ለምስኪኖች መብል ...›› በማለታቸው ጋር የተያያዘ ነው። አቢ ሰዒድ አልኹድሪይ እንዲህ ብለዋል “የአላህ መልዕክተኛ በነበሩበት ዘመን ዘካተል ፊጥር የምናወጣው ከምግብ አንድ ሳዕ ነበር” ብለዋል። ዘካተል ፊጥርን ከተገደበለት ጊዜ ማስቀደም ወይም ማቆየት እንደማይቻል ሁሉ የአወጣጡን አይነትም መቀየር አይቻልም። ዒባዳ ሁልጊዜ በአላህ የሚደነገግ እንጂ በአስተያየት ምንፈፅመው አይደለም።ማንኛዉም ሙስሊም ዒባዳው እንዳይበላሽበት ሊጠነቀቅ ይገባዋል። በገንዘብ መተመን በቀደምት ሰለፎች አልተፈፀመም።ከጥቂቶች በቀር አብዛኞቹ የኢስላም ሊቃዉንት በገንዘብ ማዉጣትን ይቃወማሉ። አል-ኢማም ማሊክ፣ አል-ኢማም አሻፊዒይ እና አል-ኢማም አህመድ ይህ መዝሀባቸው ነው። ስለዚህም በተባለው መልኩ በእህል ያወጣ ሰው በሁሉም ስምምነት ትክክለኛ ዒባዳ ሰርቷል። እያንዳንዱ ሙስሊም በጾመበት ቦታ ዘካተል ፊጥርን ማዉጣቱ ቢሆንም የሚያስፈልገው ነገር ግን ምግብ የሚቀበል ሚስኪን ሰው የሌለበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በቤተሰቦቻቸዉ ወይም ጓደኞቻቸው አማካኝነት ችግረኞች ወዳሉበት ቦታ መላክ ይችላሉ። በጥቅሉ ማንኛዉም ሰው ኢስላምን በሚገባ ለመተግበር መሞከር ይገባዋል።

تقبل الله الصّيام والقيام وجميع الطّاعات